በኮለበስ ኦሀዮ የሚገኘው የቅዱስ ጊዮርጊስ እግር ኳስ ቡድን በዚህ ስም ከመታወቁ በፊት የጣና የስፖርት ክለብ ይባል ነበር  ይህ ቡድን በከተማው በሚኖሩ ታታሪ የእስፖርቱ አፍቃሪዎች ተመስርቶ ብዙ ወጣቶችን ከማጫወቱም በላይ ወደሌላ ቦታዎችም እየተጓዘ ውድድሮችን በመካፈል ልምድንና ወዳጅነትን አጠናክሮአል 1993 ዓ/ም  የሚድዌስት የእግር ኳስ ውድድር መስራችና ተካፋይ በመሆን እስከዛሬም በብቃት በመሳተፍ ላይ ይገኛል  የቅዱስ ጊዮርጊስ  የእግር ኳስ ቡድን በ1998, 1999, 2000 እና 2002 ዓ/ም የሚድዌስት ቻምፒዮናነቱን ተቀዳጅቷል በእነዚህ ዓመታት አራቱንም ጊዜ የቅዱስ ጊዮርጊስ ተጫዋቾች የ(mvp) ማእረግ ተቀዳጅተዋል ከ 2000 ዓ/ም ጀምሮ የ(ESFNA) ዓባል ከመሆን አልፎ በዚህ የሰሜን አሜሪካ እግር ኳስ ውድድር ሁለተኛ ዲቪዚዮን ውድድሮችን ተካፍሏል በነዚህም ጊዚያት

1ኛ/ በ 2000 ዓ/ም ከዲቪዚኑ 3ኛ ደረጃን ሲቀዳጅ በጊዜው የነበረው አሰልጣኝ የአመቱ ኮከብ አሰልጣኝ በመባል ተሸልሟል

2ኛ/ በ2002 ዓ/ም የሁለተኛነትን  ደረጃ በመቀዳጀቱ ወደ አንደኛ ዲቪዚዮን ከማለፉም ባሻገር የዓመቱ የጠባይ ዋንጫ ተሸላሚ ሆኗል

የኮሎምበስ የቅዱስ ጊዮርጊስ የእግር ኳስ  ቡድን የከተማውን ኢትዮጵያውያን አክብሮትና ፍቅር ያተረፈ የዓባላቱን የአካልና የስነ ምግባር ደህንነት ያጎለመሰ ድርጅት ነው

ይህም ቡድን ሃያ አምስት ቋሚ ተጫዋቾችን ያቀፈ ሲሆን አስተዳደሩም ቡድኑ ባፈራቸው ወጣቶች የተዋቀረ ሲቀመንበር ፀሀፊ  ገንዘብ ያዥ አንድ አሰልጣኝ እና ምክትል አሰልጣኝ አሉት  ኮሚቴው  ከመላው የቡድኑ አባላትና የከተማው እስፖርት አፍቃሪ ጋር በመሆን በተቀላጠፈ መልኩ ስራውን እየሰራ የሚገኝ መሆኑን ስመግለፅ እንወዳለን

በኮለበስ ኦሃዮ የቅዱስ ጊዮርጊስ እስፖርት ክለብ